# ኢትዮጵያ ሀገራችን ባለ ብሩህ ራእዩ ታላቅና በሳል መሪዋ አጣች

በህዝባዊ አመለካከታቸው፣ በበሳል አመራራችው፣ በሆደሰፊነታቸው፣ በልማታዊነታቸውና በትግል ፅናታቸው የሚታወቁት ክቡር የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ሰኞ ነሃሴ 14/2004 ዓ.ም ከምሽቱ 5፡40 ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን የሰማነው በከፍተኛ ድንጋጤ ነው።

አቶ መለስ ለሀገር ልማት፣ ለሕዝብ ብልፅግና፣ ለሰላምና ለዲሞክራሲ ሲሉ የ19 ዓመት ወጣት ሆነው ወደትግል ሜዳ ከነጎዱበት ጊዜ ጀመሮ ራሳቸውን የህዝብ ብርሀን ሆነው እንደ ሻማ እየቀለጡ ሲያገለግሉ፣ ሲታገሉና ሲያታግሉ፤ ሲመሩና ሲያስተባብሩ በወጉና በልኩ እረፍትና መዝናናትን ሳይሞክሩ ጊዚያቸውን ሁሉ ለህዝብና ለህዝብ ብቻ የሰዉ ሀገር በቀላሉ የማትተካቸው ምርጥ የህዝብ ልጅ ነበሩ።

ሀገራችን ኢትዮጵያን ከደርግ አስከፊ አገዛዝ ነፃ ከማውጣት ጀምሮ የህዝቦችን፣ የሃይማኖቶችንና የፆታ እኩልነቶችን ያረጋገጡ በግምባታ ትግሉም ሃገራችን ትታወቅበት ከነበረው የረሃብ፣ የድንቁርናና የጦርነት አዙሪቶች በማውጣት በተለይም ላለፉት 9 ዓመታት በተከታታይ ባማካይ 10.5 % የኢኮኖሚ እድገት እንዲመዘገብ ያደረጉና ገፅታችንን በአለም ላይ የቀየሩ ብሩህ መሪ ነበሩ።

ዛሬ በኢትዮጵያችን በትምህርት፣ በጤና፣ በሃይል ምንጭ፣ በንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ በአየርመንገድ፣ በባቡር ሃዲድ፣ በገጠርና ዋና ዋና መንገዶች እንዲሁም በሱካር ልማት የሚታዩት ውጤታማ ስራዎች በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አቶ መለስ ብልህ አመራር የተከናወኑና እየተሰሩም ጭምር ያሉ ናቸው። በከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማስፋፋትን፣ የኮብል ስቶን ልማትንና ስራ ፈጠራን፣ ድሀ ተኮር የኮንዶሚንየም የቤት ልማት ማስፋፋትን፣ ልማታዊ ባለሀብት መፍጠርን፣ እንዲሁም የሃገር ውስጥና የወጪ ኢንቨስትመንት መሳብን የብልሁ ታላቁ መሪ አቶ መለስ ውርሶች ናቸው። በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ኑሮ ለመቀየርና ምርታማነትን ለማሳደግ በቴክኖሎጂና በገበያ ልማት የታገዘ የገጠር ልማት ስራ እየተከናውነ ያለው በሳቸው ጥብቅ ክትትል መሆኑ በስፋት ይታወቃል።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ይህንን አስደናቂ ልማት ለማስቀጠልና አገራችንን ወደ መካከለኛ ገቢ አገሮች ተርታ ለማሰለፍ አሁን በመተግበር ላይ ያለውን ያምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዋና ቀያሽና መሪ የነበሩ ሲሆኑ ዝንተ አለም ለም አፈራችንን እየጠረገ ሲፈስ የነበረው አባይ ወንዛችንን ለሀይል ምነጭነትና ለመስኖ እንዲውል እቀዱን የመሩና የህዳሴ ግድቡን ያስጀመሩ ቆራጥ መሪ ነበሩ።

በአህጉራችን አፍሪካ ባጠቃላይ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪቃ በተለይ ለሰላም ማስፈንና መረጋጋት ያደረጉት አስተዋፅኦ ልዩ ችሎታቸውንና ጥበባቸውን ለአለም ያሳዩበት ነበር። ኢትዮጵያ ሀገራችን በአለም የሰላም ማስከበር ተልእኮ እጅግ አሰቸጋሪ በሚባሉ አገሮች ሰራዊቷን በማሰማራት በተለይ በሩዋንዳ፣ በላይበርያ፣ በዳርፉር፣ በደቡብና ሰሜን ሱዳን አካባቢዎች ሊደርስ የነበረን አሰከፊ እልቂት በማስቀረት የተጫወቱት ሚና በአፍሪካ ህዝቦች ታሪክ ቋሚ የሰላም ቅርስ ሆኖ ሲዘከር የሚኖር ነው። ወንድም

የሶማልያ ህዝብም ሰላምና መረጋጋት እንዲያገኝ ያደረጉት ጥረትና ያስገኙት ውጤት በጣም የሚደነቅ ነው።

አቶ መለስ ሀገራችን ኢትዮጵያንና አህጉራችን አፍሪቃን በአለም መድረኮች በመወከል በአየር ንብረት ለውጥ፣ በምግብ ዋስትና፣ በድህነት ቅነሳ፣ በኢነርጂ ስርጭትና ቢኢኮኖሚ እድገት ጉዳዮች በዋና መፍትሄ ሰጪነት ያለማቋረጥ እየተጋበዙ ሀሳባቸው ሙሉ ተቀባይነትና አድናቆት እንዲያገኝ ያደረጉ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጅ ነበሩ።

ይህን ታሪክ የማይዘነጋው ስራቸውንና የኢትዮጰያ ህዳሴ እቅዳቸውን ለማስቀጠል እኛ በኖርወይ የምንኖር ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቃል እየገባን በድንገተኛ አሳዛኝ ህልፈታቸው ለቤተሰባቸውና ለኢትዮጵያ ህዝብ ልባዊ መፅናናትን እንመኛለን።

በዚህ አጋጣሚ በኖርዌይ ኗሪ ኢትዮጵያውን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የታላቁ መሪያችንን ሃዘን ለመግለፅ የሶስት ቀን ለቅሶ ተቀምጠን እንገኛለን።

**በኖርዌይ ኗሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን**